በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ.መ.ቁ 190228

ቀን ሀምሌ 26 2013ዓ.ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካቾች፡ 1ኛ. አቶ ቶፊቅ መሀመድ
2ኛ. አቶ ሽኩር ረዲ } ጠበቃ ወንድወሰን ሂርጳ ቀረቡ

ተጠሪ፡ የኢፌዲሪ የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን፡- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካቾች የፌደራል የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 00027 በ26/4/11ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 169910 በ30/4/12ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት በ19/5/12ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ተጠሪ በስር የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን የዳኝነት ችሎት በአመልካቾች ላይ ባቀረበው ክስ የግል ተበዳይ የሆነው የK.C.J ካምፓኒ ወኪል ጀሽ ወንድማማቾች ኃ/የተ/የግ/ማህበር የድርጅቱን እቃዎች ከሌሎች ለመለየት የሚያስችል EVEREST (ኤቨረስት) የሚል የማይዳሰስ ንብረት ምስል ባለቤት ነው፡፡ EVEREST የንግድ ምልክት በቃላት ብቻ ያልተገደበ የቅርጽና የምስል ነጻነትን ምናባዊ ይዘት በመፍጠር ከምርትና አገልግሎት ጋር ካለው ጥምረት አንጻር ከ1982ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ የሀገሪቱ መገበያያ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ስፍራዎች በመግባት በገነባው መልካም ስም የሸማቹ ማህበረሰብን ምርጫ የመምራት አቅም ፈጥሯል፡፡ ሆኖም የኤቨረስት የንግድ ምልክትና የአመልካቾች የምርት ማሸጊያ መጠን፤ በማሸጊያው ላይ ባረፈው የሴት ምስል እና በአብዛኛው ደረጃ አደናጋሪ ሆኖ እያለ በኢትዮጵያ ውስጥ ጥበቃ ያልተደረገለትን የምርት ማሸጊያ ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት 1ኛ አመልካች ከ2006ዓ.ም ጀምሮ ተስመስ ቆንጆ የሚባል የምርት ማሸጊያ ዲዛይን አመሳስሎ በማምረት እንዲሁም 2ኛ አመልካች የዚሁን አይነት ተመሳሳይ ምርት ከ2008ዓ.ም ጀምሮ ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት ሸማቹ ማህበረሰብን የሚያደናግር ምርት በመሸጥ ላይ የሚገኙ በመሆናቸውና የምርት ማሸጊያው እቃው ምልክት እና የሚኖረው አገልግሎት ተመሳሳይና አደናገሪ በመሆኑ ምክንያት አመልካቾች እየፈጸሙ የሚገኘው ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ተግባራቸውን እንዲያቆሙ ትእዛዝ እንዲሰጥልን እንዲሁም አመልካቾች ለፈጸሙት ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ተግባር ከአመታዊ ሽያጭ ገቢያቸው 10% እንዲቀጡ ውሳኔ እንዲሰጥልን በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡ የሰነድ እና የሰው ማስረጃዎችንም አያይዞ አቅርቧል፡፡

አመልካቾች ባቀረቡት መልስ በK.C.J ካምፓኒ ተመዝግቧል የተባለው EVEREST (ኤቨረስት) የተሰኘው የቃል የንግድ ምልክት ነው፡፡ በክሱ በምስልና በቃል ብቻ ያልተገደበ የቅርጽ ነጻነትንም ያካተተ ነው በሚል የቀረበው በማስረጃ ያልተደገፈ ነው፡፡ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱ ላይ ምስልና ቅርጹ ጥበቃ አልተሰጠውም፡፡ በንግድ ምልክትና ጥበቃ አ/ቁ 501/98 አንቀጽ 4 መሰረት የንግድ ምልክት ባለቤትነት የሚገኘውና በ3ኛ ወገን ላይ ተፈጻሚነት የሚኖረው ሲመዘገብና የምስክር ወረቀት ሲሰጥ ነው፡፡ K.C.J ካምፓኒ የተጣሰበት የጸጉር ማቅለሚያ ሂና ማሸጊያ ምስልና ቅርጽ ላይ መብት የለውም፡፡ በአ/ቁ 813/2006 አንቀጽ 8(1)፤ 8(2) ሀ እና ለ መሰረት ያልተገባ የንግድ ውድድር አለ የሚባለው ከሀቀኝነት ውጪ የማታለል ስራ፤ የተወዳዳሪን ጥቅም ሊጎዳ የሚችል ተግባር መፈጸም ፤የማደናገር ተግባር እንዲሁም የማደናገር ድርጊት ወይም የሌላውን ነጋዴ መረጃ ማውጣት እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ ሆኖም አመልካቾች በህጋዊ የምዝገባ ሂደት ባገኙት ህጋዊ የንግድ ምልክት እቃዎችን ከመሸጥ ባለፈ የፈጸሙት ህገወጥ ድርጊት ስለመኖሩ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ የቀረበው ክስ አመልካቾች በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ ለማድረግና ተጠሪ በመስኩ ብቸኛ ነጋዴ ሆኖ ለመቆየት አልሞ ያቀረበው በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡ ክስ የተነሳበት ምርት በማሸጊያው ላይ ያለው ምስል እና ቅርጽ ለጥበቃ ብቁ አይደለም፡፡ በአመልካቾች የንግድ እቃዎች ጥቅም ላይ የዋሉት ተስመስ ቆንጆ እና መልካማ የተሰኙት የንግድ ምልክቶች የምዝገባ የምስክር ወረቀት ያገኙና ህጋዊ ጥበቃ ያላቸው ናቸው፡፡ ተስመስ ቆንጆ፤ ኤቨረስት እና መልካማ በሚሉት የንግድ ምልክቶች መካከል የአጻጻፍም ሆነ በትርጉም ሊያሳስት የሚችል ተመሳሳይነት የለም፡፡ የጸጉር ማቅለሚያ ሂናዎችን የሚጠቀሙ አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ያላቸውና የሚፈልጉትን የምርት አይነት ለይተው የሚያውቁ እንደሆኑ ይገመታል፡፡ ስለሆነም በንግድ ምልክቶቹ መካከል መመሳሰል የሌለ በመሆኑ ሸማቹን አያደናግርም፡፡ ተጠሪ ያቀረበው የውጪ ሀገር የምዝገባ ምስክር ወረቀት በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት እስካልተመዘገበ ድረስ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፡፡ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የሰጣቸው ማብራሪያዎች በአዋጁ እንዲያስፈጽመው ከተሰጠው ስልጣን ጋር የማይሄድ ከመሆኑም በተጨማሪ የንግድ ምልክቶች ያደናግራሉ

ወይም አያደናግሩም ብሎ የመወሰን ስልጣን የአንድ አስፈጻሚ ስልጣን ሳይሆን የፍርድ ቤቶች ስልጣን ነው፡፡ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በመ.ቁ 145383 በ24/8/10ዓ.ም አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ በመሆኑ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ጠይቀዋል፡፡ የሰነድ እና የሰው ማስረጃዎችንም አያይዘው አቅርበዋል፡፡

ችሎቱም 1ኛ. አመልካቾች አ/ቁ 813/2006 አንቀጽ 8(1) እና 8(2)(ሀ) እና (ለ)ን በመተላለፍ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ፈጽመዋል ወይስ አልፈጸሙም? 2ኛ. አመልካቾች ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ፈጽመዋል የሚባል ከሆነ ሊሰጥ የሚገባው ዳኝነት ምን መሆን አለበት? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ግራቀኙን በቃል ካከራከረ፤ የግራቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ በንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ አ/ቁ 813/2006 አንቀጽ 8(1) ማንኛውም ነጋዴ በንግድ ስራ ሂደት ውስጥ ማናቸውም ሀቀኛ ያልሆነ፤ አሳሳች ወይም አታላይነት ያለበትና የተወዳዳሪን የንግድ ጥቅም የሚጎዳ ወይም ሊጎዳ የሚችል ተግባር መፈጸም እንደማይችል ከደነገገው አንጻር በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የግል ተበዳይ ብሎ ያቀረበው የK.C.J ካምፓኒ ወኪል ጆሽ ወንድማማቾች ኃ/የተ/የግ/ማህበር የጸጉር ማቅለሚያ ምርቶችን ከውጪ እያስመጣ የሚሸጥ ሲሆን ለምርቱ የንግድ ምልክት የቃል ጥበቃ ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በ1/9/08ዓ.ም ተሰጥቶታል፡፡ በተመሳሳይ 1ኛ አመልካች TSMSSKONJO የሚል የቃልና የምስል የንግድ ምልክት ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በ22/9/08ዓ.ም እንዲሁም 2ኛ አመልካች MELKAMA የሚል የቃል የንግድ ምልክት በ4/10/08ዓ.ም ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ጥበቃ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት የንግድ ስራቸውን እያከናወኑ ያሉትም ይህንኑ የንግድ ስማቸውን እየተጠቀሙ መሆኑን አመልካቾች ያቀረቡ ሲሆን ተጠሪም ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ ይህንኑ የሚያረጋግጥ በመሆኑ ከዚህ አንጻር አመልካቾች ተጠሪ ጥበቃ ያገኘበትን EVEREST የሚል የንግድ ምልክት እንዳልተጠቀሙ ያስገነዛባል፡፡

ግራቀኙ ካቀረቡት ክርክር አንጻር ተጠሪ በተባለው የምርት ማሸጊያ ላይ ሌሎች እንዳይጠቀሙበት ለመከልከል እና በብቸኝነት ለመጠቀም የሚያስችል መብት አላቸው ወይስ የላቸውም? የሚለው ነጥብ ሲታይ በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አ/ቁ 501/98 መሰረት የንግድ ምልክት ምዝገባ ያገኘ ማንኛውም ባለመብት ሌላ 3ኛ ወገን በንግድ ምልክቱ እንዳይጠቀም ለማገድ መብት እንደሚያስገኝለት ከደነገገው አንጻር በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ለምርቱ መለያ በንግድ ምልክትነት ያስመዘገበው የምርቱን ስያሜ የሚያመላክት Everest የሚል ቃል እንጂ የምርት ማሸጊያውን ዲዛይን እና በምርቱ ላይ ያለውን ምስል አይደለም፡፡ ምንም እንኳ የተጠሪ ምስክሮች የማሸጊያ ዲዛይኑና ምስሉ ተመዝግቦልናል ያሉ ቢሆንም ተጠሪ ይህን የሚያስረዳ የሰነድ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ ተጠሪ ያቀረበው ማስረጃም Everest የሚል የቃል ጥበቃ ያገኘበትን የምዝገባ የምስክር ወረቀት ነው፡፡ ሌላው ተጠሪ ያቀረበው ማስረጃ ከህንድ ሀገር የተሰጠ የጥበቃ ሰርተፍኬት በኢትዮጵያ ውስጥ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ቀርቦ ያልጸደቀ በመሆኑ ህጋዊ ማስረጃ ነው ተብሎ አይወሰድም፡፡ በአንጻሩ አመልካቾች እና የአመልካቾች ምስክሮች ማሸጊያው የወል ወይም የጋራ መጠቀሚያ መሆኑን መስክረዋል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በ3ኛ ወገኖች ላይ ክስ ሊያቀርብ የሚችለው ጥበቃ ያገኘበት የቃል የንግድ

ምልክት ተጥሶ ሲገኝ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ተጠሪ አመልካቾች Everest የሚለውን የቃል የንግድ ምልክት እየተጠቀሙ የጸጉር ማቅለሚያ ምርትን ለገበያ እያቀረቡ ስለመሆኑ አላስረዳም፤ በሌላ በኩል አመልካቾች ለምርቱ እየተጠቀሙ የሚገኙት TSMSSKONJO እና MELKAMA የሚሉ መጠሪያዎችን በመጠቀም መሆኑን የተጠሪ እና የአመልካቾች ምስክሮች አስረድተዋል፡፡

የአመልካቾች ድርጊት ሸማቹን ያደናግራል ወይስ አያደናግርም የሚለውን ነጥብ በተመለከተ በዋናነት የጸጉር ማቅለሚያ የሚጠቀመው የህብረተሰብ ክፍል የትኛው ነው የሚለው ሲታይ የተጠሪ ምስክሮች ሁሉም አይነት ሸማች ምርቱን ይጠቀመዋል ያሉ ሲሆን የአመልካቾች ምስክሮች የጸጉር ማቅለሚያ መሰረታዊ የሚባል ሳይሆን የቅንጦት እቃ ነው፤ ምርቶቹንም የሚጠቀሙት የህብረተሰብ ክፍሎች በአብዛኛው የተሻለ የግንዛቤ ደረጃ ያላቸውና ምርቶችን በማሸጊያው ብቻ አይተው የሚገዙ ሳይሆን በስም ለይተው የሚገዙ ናቸው የሚል መከራከሪያ አቅርበዋል፡፡ በዚህ ረገድ ምርቱን የሚጠቀሙት የህብረተሰብ ክፍሎች ወይም ሸማቾች የትኞቹ ናቸው የሚለው ሲታይ የጸጉር ማቅለሚያ መሰረታዊ ፍላጎትን ለማማላት የሚውል ምርት ሳይሆን ለተጨማሪ ውበት መጠበቂያነት የሚውል እንደመሆኑ ምርቱን የሚጠቀሙት የህብረተሰብ ክፍሎች በሚጠቀሙት ምርት ምንነት ላይ ግንዛቤ ያላቸው መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የሚፈልጉትን ምርት በስም ለይተው ለመግዛትና ለመጠቀም የሚችሉ ናቸው፡፡ ተጠሪም ቢሆን የአመልካቾች ድርጊት ሸማቹን የሚያደናገር ነው ከማለት በስተቀር ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡ ስለሆነም የአመልካቾች ድርጊት ሸማቹን የሚያደናግር ድርጊት ነው የሚባል ባለመሆኑ አመልካቾች የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ አ/ቁ 813/2006 አንቀጽ 8(2)(ሀ)ን በመተላለፍ የፈጸሙት ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር የለም፤ በመሆኑን ወደ ሁለተኛው ጭብጥ መግባት ሳያስፈልግ ተጠሪ አመልካቾች ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ፈጽመዋል በሚል ያቀረበውን ክስ በማስረጃ ስላላስረዳ በማለት ክሱን ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

ተጠሪ ከላይ በተገለጸው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌደራል የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የግራቀኙ ክርክርን የበለጠ ግልጽ ለማድረግ ከኢእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ያለው የጽ/ቤቱ የንግድ ምልክትና ኢንዱስትሪ ንድፍ ልማት ጥበቃ ዳይሬክቶሬት የንግድ ምልክት ምርመራ ከፍተኛ ባለሙያ እንዲቀርብ በማድረግ ምዝገባ ሳያደርግ የመጠቀም መብትን በሚመለከት ሙያዊ ምስክርነት እንዲሰጥ ከፍ/ቤቱ ለቀረበለት የማጣሪያ ጥያቄ ባለሙያው የሰጠውን ምላሽ ተቀብሎ እንዲሁም በስር ፍ/ቤት በማስረጃ ዝርዝር ፊደል (ለ) ላይ የተገለጸው ኤግዚቢት በፍ/ቤት ቀርቦ እንዲታይ ካደረገ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍ/ቤት የተጠሪን ክስ ውድቅ በማድረግ ለደረሰበት ድምዳሜ መነሻው ተጠሪ የንግድ ምልክት ጥበቃ ያገኘው ኤቨረስት በሚል ስም ሲሆን በተመሳሳይ የንግድ ዘርፍ ተሰማርተው ማደናገር ፈጽመዋል የተባሉት የአመልካቾች ድርጅት ስም ደግሞ ቆንጆ እና መልካማ የሚል መጠሪያ ነው ያላቸው፤ ስለዚህ ስማቸው ኤቨረስት ከሚለው ስም ጋር ምንም አሳሳች ነገር የለውም፤ በተጨማሪም ይህን የጸጉር ማቅለሚያ ምርት የሚጠቀሙ ሸማቾች ከመደበኛ ማህበረሰብ የተሻለ ግንዛቤ እና አቅም ያላቸው በመሆኑ የሚገዙትን ምርት በሚገባ የተረዱ ናቸው፡፡ ስለዚህ በምርቱ ዙሪያ መደናገር አይገጥማቸውም፤ የምርቱ ማሸጊያ መልክና ቀለም ምዝገባ ያልተሰጠው በመሆኑ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ጥበቃ አለው ሊባል አይችልም በሚል ነው፡፡ በስር ፍ/ቤቱ የተሰሙት የተጠሪ ምስክሮች የኤቨረስት የጸጉር ቀለም ማሸጊያ ከቆንጆና መልካማ የጸጉር ቀለም ማሸጊያ ጋር በጣም የሚመሳሰል በመሆኑ በሸማቾች ላይ ማደናገር እያስከተለ መሆኑን እንደ አንድ ሸማች ጭምር እንደሚያውቁ እና ሸማቾችም ችግር እንደገጠማቸው እንደገለጹላቸው መስክረዋል፡፡ በሌላ በኩል ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በቁ. አጠ28/662-11 በ26/12/08ዓ.ም ለአዲስ አበባ ፓሊስ እንዲሁም በቁ. አጠ28/119-660/08 በ26/12/08ዓ.ም እና በቁ. አጠ28/560-104/08 በ1/11/08ዓ.ም ለንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ዋና ባለስልጣን በዋና ዳይሬክተሩ የተጻፉት ደብዳቤዎች የኤቨረስት የጸጉር ቀለም ማሸጊያ ከቆንጆና መልካማ የጸጉር ቀለም ማሸጊያ ጋር አብሮ ቀርቦ ቢታይ በአብዛኛው በሚባል ደረጃ የመጠን፤ የፊደላት ቀለማትና በአጻጻፍ ዘዴ በመደቦች ቀለማት፤ በማሸጊያው ላይ ባረፈው የሴት ምስል… እንዲሁም በአጠቃላይ የቀለም ቅንጀት ተመሳሳይ በመሆኑ በገበያ ውስጥ ቢገባ ሸማቹን ሊያደናግር እንደሚችል በዚህም ምክንያት የአንድ ድርጅት ምርት እንደሚመስሉ ይገልጻሉ፡፡

ተጠሪ ባቀረበው ክስ በአ/ቁ 813/2006 አንቀጽ 8(2)(ሀ) መሰረት መደናገር በስም ብቻ ሳይሆን በማናቸውም ሁኔታ ስለመሆኑ፤ እንዲሁም ኤቨረስት የጸጉር ቀለም የምርቱን ማሸጊያ ከ1982ዓ.ም ጀምሮ ከቆንጆ እና መልካማ በፊት በቀደምትነት የሚጠቀምበት በመሆኑ በመጠቀም የጥበቃ መብት አለኝ በማለት የተከራከረ ሲሆን በአመልካቾች በኩል ደግሞ ጥበቃ የሚገኘው በአ/ቁ 501/98 አንቀጽ 4 መሰረት በማስመዝገብ ስለሆነ ያልተመዘገበ የንግድ ምልክት ሌላው እንዳይጠቀምበት ለመከላከል የሚያስችል መብት አይሰጥም በሚል ተከራክሯል፡፡ ሆኖም በስር ፍ/ቤቱ በጽሁፍ ማስረጃነት ከአእምሯዊ ንብረት ምዝገባ ጽ/ቤት በቁ. አጠ28/560-104/08 በ1/11/08ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በንግድ ምልክት ላይ ያለ መብት በመሰረታዊ ደረጃ ከመመዝገብ የሚመነጭ ቢሆንም ሳይመዘገብ ለረጅም ግዜ ግልጋሎት ላይ የዋለ የንግድ ምልክትም ቢሆን ለባለቤቱ መብትን የሚያጎናጽፍ መሆኑ በንግድ ምልክት አዋጁ ላይ የተለያዩ ቦታዎች ተጠቅሶ እንደሚገኝ እና የንግድ ምልክት ህግ ሳይንስም ይህን እንደሚያረጋግጥ የተመለከተ መሆኑን ይገልጻል፡፡ በተጨማሪም በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በማጣሪያ ምስክርነት የቀረቡት ባለሙያ ይህንኑ ሃሳብ በሚያጠናክር መልኩ የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ አንጻር የኤቨረስት የጸጉር ቀለም ማሸጊያ ባለቤት K.C.J ካምፓኒ ከ1982ዓ.ም ጀምሮ በማሸጊያው ይጠቀም እንደነበር ሲታይ በ2006ዓ.ም እና 2008ዓ.ም የኤቨረስት ባለቤት K.C.J መብት እንዳለው ያስገነዝባል፡፡ በኤግዚቢትነት ለፍ/ቤቱ የቀረቡት የኤቨረስት፤ የመልካማ እና የቆንጆ የጸጉር ቀለም መያዣ ምርቶች ማሸጊያዎች ፍ/ቤቱ እንደተመለከተው ከስማቸው መለያየት በስተቀር በሌላው ይኀውም በማሸጊያው መጠን፤ የፊደላት ቀለማት፤ የመደቦች ቀለማት፤ የማሸጊያው ቀለም፤ በማሸጊያው ላይ ያረፈው ፎቶ… ተመሳሳይነት እንዳለው እና አንዱን ከአንዱ ለመለየት አስቸጋሪ መሆኑን ያስገነዛባል፡፡

የአመልካቾች ምስክሮች የጸጉር ማሸጊያ ቢመሳሰሉም የፈለጉትን የምርት አይነት በስሙ ለይተው መግዛት እንደሚቻል የገለጹ ሲሆን 3ኛ ምስክራቸው የተጠሪ የጸጉር ቀለም ማሸጊያ ከአመልካቾች የጸጉር ቀለም ማሸጊያ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ የሚመሳሰሉ እና በዚሁ ምክንያትም ሊያደናግሩ እንደሚችሉ እንደሚያደናግሩ የገለጹ ከመሆኑም በተጨማሪ ከላይ የተገለጹት የአእምራዊ ንብረት ጽ/ቤት በተለያዩ ቀናት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በጻፋቸው ደብዳቤዎች ላይ የአመልካቾች የምርት ማሸጊያ ከተጠሪ የምርት ማሸጊያ ሙሉ በሙሉ የሚመሳሰሉ እና ሸማቹንም የሚያናግሩ፤ ሊያደናግሩ የሚችሉ መሆኑን ዝርዝር ማብራሪያ ገልጿል፡፡ ሆኖም የስር ፍ/ቤት ይህን የጽሁፍ ማስረጃ ለምን እንዳልመዘነው ወይም እንዳልተቀበለው በውሳኔው ላይ አልገለጸም፡፡ በአመልካቾች በሰነድ ማስረጃነት የቀረቡትን በወንጀል ጉዳይ የተሰጡትን ውሳኔዎች በተመለከተ የወንጀልና የአስተዳደራዊ ጉዳዮች የማስረጃ ምዘና የሚለያይ ከመሆኑም በተጨማሪ በወንጀል ነጻ መባል ከአስተዳደራዊ ተጠያቂነት ነጻ እንደማያደርግ የወንጀል መርህ ከደነገገው አንጻር ማስረጃው ሚዛን የሚደፋ ሆኖ አልተገኘም፡፡

የስር ፍ/ቤቱ የምርቱ ተጠቃሚዎች የተሻለ ግንዛቤ ያላቸው ያላቸው በመሆኑ በምርቱ ማሸጊያ መመሳሰል መደናገር አይኖርም የሚለው መደምደሚያ የሀገሪቱን ማህበረሰብ ተጨባጭ ሁኔታ ያላገናዘበ እና በጥናት ላይ ያልተመሰረተ በግለሰብ ሀሳብ ላይ ብቻ የተመሰረተ ከመሆኑ አንጻር፤ የተሻለ አረዳድ ያለው የመንግስት መስሪያ ቤት የሰጠውን መረጃ ሳይመዝን የደረሰበት በመሆኑ እንዲሁም የአ/ቁ 813/2006 አንቀጽ 8(2)(ሀ)ን ድንጋጌ መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ተጠሪ ክሱን በሚገባ አላስረዳም ሲል የሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም፡፡ ስለሆነም በተጠሪ በስር ፍ/ቤት በቀረቡት የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በኤግዚቢትነት ባስቀረባቸው ምርቶች እና የባለሙያ ምስክርነት አመልካቾች በአ/ቁ 813/2006 አንቀጽ 8 (1) እና 2(ሀ) የተደነገገውን በመጣስ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር የፈጸሙ መሆናቸውን ተጠሪ በበቂ ማስረጃ ያስረዳ ስለሆነ አመልካቾች ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር  ተግባር ፈጽመዋል በማለት እንዲሁም አመልካቾች ጥፋተኞች ናቸው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በመሆኑም የስር የዳኝነት ችሎቱ የተጠሪን ክስ ውድቅ በማድረግ የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት ከተቀበለ በኋላ በአ/ቁ 813/2006 አንቀጽ 42(3) መሰረት አመልካቾች እያንዳንዳቸው የአመታዊ የሽያጭ ገቢያቸውን 5%(አምስት በመቶ) የገንዘብ ቅጣት እንዲቀጡ በማለት ወስኗል፡፡ እንዲሁም የአመልካቾች ድርጅቶች የሚጠቀሙበት የጸጉር ቀለም ማሸጊያዎች ከኤቨረስት የጸጉር ቀለም ማሸጊያ በመጠን፤ በፊደላት፤ ቀለማትና በአጻጻፍ ዘዬ፤ በመደቦች ቀለማት፤ ማሸጊያው ላይ ባረፈው የሴት ምስል …. በአጠቃላይ የቀለሞች ቅንጅት ተመሳሳይነት ያለው በመሆኑ በገበያ ውስጥ ሸማቾችን የሚያደናግርና ሊያደናግር ስለሚችል እንዳይጠቀሙ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካቾች ከላይ በተገለጸው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ በንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ አ/ቁ 813/2006 መሰረት አመልካቾች የማደናገር ሁኔታ ያስከተለ ተግባር ፈጽመዋል አልፈጸሙም የሚለው የማስረጃ ጉዳይ በመሆኑ የባለስልጣኑ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በቁ. አጠ28/662-11 በ26/12/08ዓ.ም ፤ በቁ. አጠ28/119-660/08 በ26/12/08ዓ.ም እና በቁ. አጠ28/560-104/08 በ1/11/08ዓ.ም የተጻፋትን ደብዳቤዎች፤ ከንግድ ምልክትና ኢንዱስትሪ ንግድ ልማት ጥበቃ ዳይሬክቶሬት ባለሙያ የሰጠውን ምስክርነት እና ምርቶችን በኤግዚቢትነት በማስቀረብ የ EVEREST የጸጉር ቀለም ማሸጊያ ከቆንጆና መልካማ የጸጉር ቀለም ማሸጊያ በአብዛኛው ደረጃ የመጠን፤ የፊደላት፤ ቀለማትና የአጻጻፍ ዘዴ በመደቦች ቀለማት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በማሸጊያው ላይ ባረፈው የሴት ምስል... ተመሳሳይ መሆናቸውን ያረጋገጠ መሆኑን ከችሎቱ ውሳኔ መረዳት የተቻለ በመሆኑ የባለስልጣኑ ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካቾች የአ/ቁ 813/2006 አንቀጽ 8(1) እና 8(2) ሀ እና ለን በመተላለፍ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ፈጽመዋል በማለት የአመታዊ ሽያጭ ገቢያቸውን 5%(አምስት በመቶ) የገንዘብ ቅጣት እና አመልካቾች የሚጠቀሙበትን የጸጉር ቀለም ማሸጊያዎች እንዳይጠቀሙ መወሰኑ አግባብ ነው በማለት የስር የፌደራል የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከላይ የተገለጹትን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ ተጠሪ አላግባብ ተበዳይ ነኝ ያለው የኬሲጄ ካምፓኒ ያስመዘገበውን EVEREST በሚለው የጸጉር ቀለም ምርት ላይ የተረጋገጠለትን መብት የስር ፍ/ቤት ሳያረጋግጥ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ፈጽማችኋል በማለት የሰጠው ውሳኔ፤ ለክርክር መነሻ የሆነውን ምስል እና ማሸጊያ እንዳንጠቀም እንዲሁም አመልካቾች እያንዳንዳችን የአመታዊ ሽያጫችንን 5% እንድንቀጣ የተሰጠው ውሳኔ ተሽሮ የስር የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን የዳኝነት ችሎት የሰጠው ውሳኔ እንዲጸናልን፤ ወጪና ኪሳራም እንዲከፈለን እንዲወሰንልን የሚል ነው፡፡

ይህ አቤቱታቸው በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ አመልካቾች አከራካሪው የንግድ ምልክት በህጋዊ አካል ተመዝግቦላቸው ባለበት እና ምንም ተቃውሞ ባልቀረበበት ሁኔታ፤ የንግድ ስራቸውን እየሰሩ ባለበት ሁኔታ፤ ከሌላው ተመሳሳይ የንግድ ምልክት ካለው በተለየ እነሱ ብቻ ተለይተው የንግድ ስራ መስራት አትችሉም የተባለበት ከአዋጁ አንቀጽ 2፤ 12 እና 4 እንዲሁም ከህገመንግስቱ አንቀጽ 41(1) አንጻር ለማጣራት ለሰበር ችሎቱ ይቅረብ ተብሎ በ15/11/12ዓ.ም በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎ ተጠሪ በ17/2/13ዓ.ም በተጻፈ ባቀረበው መልስ የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ አ/ቁ 813/2006 አንቀጽ 8(2)(ሀ) ማንኛውም ነጋዴ በሌላው ነጋዴ ወይም በነጋዴው ተግባራት በተለይም ነጋዴው ከሚያቀርበው የንግድ እቃ ጋር በተገናኘ ሁኔታ ማደናገርን ያስከተለ ተግባር ወይም ሊያስከትል የሚችል ማንኛውም ድርጊት መፈጸም እንደማይችል ከደነገገው አንጻር የስር የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካቾች የ K.C.J ካምፓኒ ለረዥም አመታት ሲጠቀምበት የነበረውን ማሸጊያ ሆን ብለው በምስልና በዲዛይን በማሳሰል ማቅረባቸውን በስር የዳኝነት ችሎቱ ከቀረቡት ከተሰሙት የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች፤ በባለስልጣኑ የይግባኝ ሰሚ ችሎት ዘንድ በኤግዚቢትነት ከቀረቡት ምርቶች እና የባለሙያ ምስክርነት በማረጋገጥ ይህም ሀቀኛ ያልሆነ አሳሳችና የተወዳዳሪን ጥቅም የሚጎዳ ሸማቹንም የሚያሳስት ተግባር ነው በማለት አመልካቾች ከዚህ ተገቢ ካልሆነ የንግድ ውድድር ድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ሲል የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግ በማለት ጠይቋል፡፡

አመልካቾች በ17/3/13ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ፤ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢዎቹ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር የስር የፌደራል የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍ/ቤት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

1ኛ አመልካች የምዝገባ የምስክር ወረቀት ያገኘበት ተስመስ ቆንጆ( TSMSSKONJO) የተሰኘው የጸጉር ቀለም የንግድ ምልክት እና 2ኛ አመልካች የምዝገባ የምስክር ወረቀት ያገኘበት መልካማ( MELKAMA) የተሰኘው የጸጉር ቀለም የንግድ ምልክት ብቻ ሆኖ ሳለ ለጸጉር ቀለማቱ የሚጠቀሙት ማሸጊያዎች በተጠሪ በተወከለው የግል ተበዳይ K.C.J ካምፓኒ ካስመዘገበው EVEREST ከተሰኘው የጸጉር ቀለም ማሸጊያ በሁሉም መልኩ ይኀውም በቅርጽ፣ በመጠን፣ በፊደላት፣ በቀለማትና በአጻጻፍ ዘዴ እንዲሁም በማሸጊያው ላይ ባለው የሴት ምስል የሚመሳሰሉ እና ሸማቹን ህብረተሰብ የሚያደናግሩ እና ሊያደናግሩ የሚችሉ መሆናቸውን በዚህም የተነሳ የንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ አ/ቁ 813/2006 አንቀጽ 8(1) ማንኛውም ነጋዴ በንግድ ስራ ሂደት ውስጥ ማንኛውም ሀቀኛ ያልሆነ፣ አሳሳች፣ ወይም አታላይነት ያለበት እና የተወዳዳሪን የንግድ ጥቅም የሚጎዳ ወይም ሊጎዳ የሚችል ድርጊት ለመፈጸም የማይችል ስለመሆኑ የደነገገውን እንዲሁም የአዋጁ አንቀጽ 8(2) ሀ እና ለ በሌላው ነጋዴ ወይም በነጋዴው ተግባራት በተለይም ነጋዴው ከሚያቀርበው የንግድ እቃ ወይም አገልግሎት ጋር በተገናኘ ሁኔታ ማደናገርን ያስከተለ ወይም ሊያስከትል የሚችል ማንኛውም ድርጊት፣ የመረጃው ባለቤት ከሆነው ነጋዴ ፈቃድ ውጪ ከሀቀኛ የንግድ አሰራር ተጻራሪ በሆነ ሁኔታ የሌላውን መረጃ የማውጣት፣ የመያዝ ወይም የመጠቀም ማናቸውም ድርጊት ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ሆነው እንደሚቆጠሩ የደነገጉትን በመተላለፍ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር የፈጸሙ ስለመሆናቸው ማስረጃዎችን የመስማት፣ የመመርመር እና የመመዘን በህግ ስልጣን የተሰጠው የፌደራል የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍ/ቤት በስር የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን የዳኝነት ችሎት ዘንድ የተሰሙትን የግራቀኙን ምስክሮች ቃል፣ ከሌሎች የሰነድ ማስረጃዎች በተጨማሪ ኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በቁ. አጠ28/662-11 በ26/12/08ዓ.ም፣ በቁ. አጠ28/119-660/08 በ26/12/08ዓ.ም እና በቁ. አጠ28/560-104/08 በ1/11/08ዓ.ም የጻፋቸውን ደብዳቤዎች በመመርመር እና በመመዘን እንዲሁም አከራካሪዎቹን EVEREST፣ ተስመስ ቆንጆ እና መልካማ የተሰኙትን የጸጉር ቀለም ምርቶች ማሸጊያዎች በኤግዚቢትነት በማስቀረብ እና በመመልከት የምርቶቹ ማሸጊያዎች ከስማቸው መለያየት በቀር በማሸጊያው መጠን፣ የፊደላት ቀለማት፣ የመደቦች ቀለማት፣ የማሸጊያው ቀለም፣ በማሸጊያው ላይ ያለው ፎቶ... ተመሳሳይነት ያለው እና አንዱን ከአንዱ ለመለየት የሚያስቸግሩ መሆናቸውን ግንዛቤ በመውሰድ፣ በተጨማሪም ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ያለውን የጽ/ቤቱን የንግድ ምልክት እና ኢንዱስትሪ ንድፍ ልማት ጥበቃ ዳይሬክቶሬት የንግድ ምልክት ምርመራ ከፍተኛ ባለሙያ በማስቀረብ እና ምዝገባ ሳያደርግ የመጠቀም መብትን በሚመለከት የሙያ ምስክርነቱን እንዲሰጥ በማድረግ የሰጠውን የምስክርነት ቃል በመመርመር እና በመመዘን አመልካቾች ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር የፈጸሙ መሆናቸውን በፍሬነገር ደረጃ በማረጋገጥ ፣ የስር የዳኝነት ችሎቱ የተጠሪን ክስ ውድቅ በማድረግ የሰጠውን ውሳኔ በመሻር አመልካቾች ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ፈጽመዋል፣ ጥፋተኞች ናቸው በማለት የንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ አ/ቁ 813/2006 አንቀጽ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

42(3) የአዋጁን አንቀጽ 8 ድንጋጌዎች የተላለፈ ማንኛውም ነጋዴ የአመታዊ ሽያጭ ገቢውን ከ5% እስከ 10% የገንዘብ ቅጣት የሚቀጣ ስለመሆኑ በደነገገው መሰረት የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት ከተቀበለ በኋላ እያንዳንዳቸው አመልካቾች የአመታዊ ሽያጭ ገቢያቸውን 5% የገንዘብ ቅጣት እንዲቀጡ በማለት የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የአመልካቾች ድርጅቶች የሚጠቀሙት የጸጉር ቀለም ማሸጊያ ከኤቨረስት የጸጉር ቀለም ማሸጊያ በመጠን፣ በፊደላት፣ በቀለማት እና በአጻጻፍ ዘዴ፣ በመደቦች ቀለማት፣ በማሸጊያው ላይ ባረፈው የሴት ምስል... በጥቅሉ በቀለሞች ቅንጅት ተመሳሳይነት ያለው በመሆኑ በገበያ ውስጥ ሸማቾችን የሚያደናገርና ሊያደናገር ስለሚችል እንዳይጠቀሙ በማለት የሰጠውን ውሳኔ፣ ይህንኑ ውሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማጽናት የሰጠውን ውሳኔ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት የፌደራል ፍ/ቤቶች አ/ቁ 1234/2013 አንቀጽ 10(1) እና የኢፌዲሪ ህገመንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) ከደነገጉት አንጻር መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘውም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 00027 በ26/4/11ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 169910 በ30/4/12ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ የሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
4. በሰበር አጣሪ ችሎቱ በ15/11/12ዓ.ም የኢፌዲሪ የንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን በቁጥር አ/ም/ክስ/አ/ዳ/199/2012 ጥር 26 ቀን 2012ዓ.ም ለጉምሩክ ኮሚሽን የሰጠው ትእዛዝ ከመፈጸም ለግዜው ታግዶ እንዲቆይ የሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
5. በዚህ የሰበር ችሎት በ12/12/12ዓ.ም በንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን ዳኝነት ችሎት በመ.ቁ 000103 የተጀመረው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
6. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም